ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞ ቅጽ 39 ቁ. 4 የካቲት 2006 ዓ.ም

# ለዳግማዊ የካቲት ሕዝባዊ አመፅ እንነሳ

የየካቲት 66 አብዮታዊ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህና ደማቅ ሚና ያለው ክስተት ነው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዝንተ ዓለም የሚያስበው የሚዘከረው ኹነት ነው። የአገዛዞች ጭቆናና ብዝበዛ መጠን እጅግ አድጎ ዜጎች መኖር የማይችሉበት ሁኔታ ሲከሰት የሕዝብን ቁጣና ብሶት ያዘለ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሊፈነዳ እንደሚችል የሕብረተሰብ ሕግ ይደነግጋል። በዓለም ላይ አስከፊ አገዛዞችን ያርበደበዱና ከሥልጣን ያስወገዱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች በጣም በርካታ በመሆናቸው ዝርዝሩን ማቅርብ አስቸጋሪ ቢሆንም በ19ኛውና በሃያኛው ክፍለ ዘመን የተከሰቱትን የፈረንሳዩንና የሩሲያ አብዮቶች፤ በ1989-90 ዓም በምስራቅ አውሮፓ አምባገነን አገዛዞች ያስወገዱትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም በ2010-12 የአረብ የጸደይ እንቃስቃሴ የሚል ስያሜ የተሰጣቸውና በተለያዩ የአረብ አገሮች ተቀጣጥለው አምባገነን አገዛዞችን ያስወገዱትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። በአገራችን በየካቲት 66 የተከሰተው አብዮታዊ እንቅስቃሴ በዓለም ውስጥ ከነበሩት አብዮቶች የተለየ ባይሆንም በወቅቱ ለ50 ዓመታት ያህል ስር ሰዶ የነበረውንና ማንም ሊያነቃንቀው የማይችልና መለኮታዊ ኃይል ነው ተብሎ ሲፈራ የነበረውን የአጼውን ሥርዓት ገዝግዞና አዳክሞ ከሥልጣን እንዲወገድ በማድረጉ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አቢይ ምዕራፍ ይዞ ይኖራል።

ዘንድሮ 40 ዓመቱን ያስቆጠረው የየካቲት 66 አብዮታዊ እንቅስቃሴ የተከሰተው በግብታዊነት ነው። እንቅስቃሴውን ቀደም ብሎ የተነበየ ወይም የገመተ አልነበረም። በኢሕአፓ ዙሪያ የተሰለፉትና ሌሎች አብዮታዊ ኃይሎች በሂደቱ የጎላ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው የታወቀ ይሁን እንጅ እንቅስቃሴውን ያቀደ፤ ያቀነባበረ ወይም የመራ ኃይል ያልነበረ መሆኑ አከራካሪ አይደለም። ለዚህም ነው በግብታዊነት ፈነዳ የሚባለው። የእንቅስቃሴውን ወቅትና ሂደት የተነበየ አይኑር እንጅ ያልተጠበቀ አልነበረም። የኢሕአፓ መሥራች የሆኑት ምሁራን በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሁኔታ እንዳለና መሪ ፓርቲ ለመመሥረት የሚያስችል ሁኔታ እንዳለ አስቀድመው አመላክተው ነበር። በተለይም ደግሞ በወቅቱ የለውጥ አብዮት ከብዙ ትውልድ በኋላ መነሳት ያለበት ጉዳይ ነው በሚል በአንዳንዶች በተለይም መኢሶንን በፈጠሩት ቡድኖች ሲስተናገድ የነበረውን የተሳሳተ ሀሳብ በመቃወምና "በሀገራችን ለውጥን ያረገዘ ሁኔታ አለ መታገል ይቻላል" በማለት በኢሕአፓ ዙሪያ የተሰባሰቡት ምሁራን ሲያቀርቧቸው የነበሩት የመከራከርያ ሀሳቦችና ድምዳሜዎች አርቆ አስተዋይነትንና ጥልቅ ግንዛቤን ያካተቱ እንደነበር የሚታበል አይደለም።

የየካቲት 66 ቱን ሕዝባዊ አመጽ የወለደው ለበርካታ ዓመታት ተጠራቅሞ የነበረው የሕዝብ ብሶትና በደል ነው፡፡ ፍንጭና ምልክቱም ቀደም ብሎ የታየ ነው፡፡ የእነ በላይ ዘለቀ፤ ቢትወደድ ነጋሽ፤ ታከለ ወልደሃዋሪያት ተቃውሞ፤ የእነመንግሥቱ ንዋይ የመንግሥት ግልበጣ ሙከራ፤ በጎጃምና በባሌ በአሩሲ የተደረጉት የአርሶ አደር አመጾች፤ የሠራተኛውና የመምህራን ተቃውሞዎች፤ የተማሪዎች አመጾች፤ የወሎው ረሃብ ያስከተለው እልቂትና በሕዝብ ላይ ያሳደረው ቁጭት የየካቲት 66ቱን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውልደት የተነበዩ መሆናቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ የየካቲት 66 እንቅስቃሴ በየካቲት ወር ውስጥ ፈንድቶ በየካቲት ወር ውስጥ ብቻ የተደመደመ አልነበረም፡፡ በየካቲት 11 ቀን 66 ተጀምሮ ሰፋት፣ ግለትና ጥንካሬን ደረጃ በደረጃ እያገኘ ያደገው ይህ ሕዝባዊ አብዮት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አስተባብሮና አካትቶ ከሰባት ወር በላይ ለፈጀ ጊዜ የተቃውሞና እምቢተኛነት አመጽ በማካሄድ በመስከረም 67 ለአጼው መንግሥት መገርሰስ ምቹ ሆኔታን ፈጥሯል፡፡

የየካቲቱን እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ልዩ ምዕራፍ የሚያሰጠውና ታሪካዊ የሚያደርገው በደል የደረሰበት የኅብረተሰብ ክፍል ሁሉ ጥቅሙን ለማስጠበቅና መብቱን ለማስከበር በአንድ ላይ መነሳቱና የበደሉ ምንጭና አራማጅ የሆነውን አስከፊ አገዛዝ ለማስወገድ ቆርጦ መነሳቱ ነው፡፡ በተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተጀመረው ይህ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በመልዕክቱ ስፋትና ጥራት፣ በትግሉ ጽናትና ተከታታይነት አንዱ ለሌላው ተምሳሌት ሆኖ በርካታውን የኅብረተሰብ ክፍል ሊስብና ሊያካትት መቻሉ በታሪክ ውስጥ ጎላ ያለ ቦታ የሚይዝ ነው፡፡ የየካቲት 66ቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ያነሳቸው ጥያቄዎችና የታገለባቸው መፈክሮች የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን መብትና ጥቅም ማስጠበቅን ከሚመለከቱና ለማኅበረሰባዊ ልዩ ልዩ ችግሮች መፍትሄ ከሚሹ ጥያቄዎች ጀምሮ ሥር ነቀል የሥርዓት ለውጥን እስከ መጠየቅ የደረሱ ጥያቄዎች ሲሆኑ በግምባር ቀደምትነት ተዋናይና ተሳታፊ የነበሩትም ከሞላ ጎደል ከሁሉም ኅብረተሰብ የተውጣጡ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡

ሠራተኛው የደሞዝ ጭማሪ፤ የሥራ ሁኔታዎች መሻሻል፤ የአሠሪና የሠራተኛ ሕግ መከበርና የመሳሰሉትን ጥያቄዎችን ይዞ ታግሏል፡፡ በ1965 ዓ.ም. ተጀምሮ የነበረው የባንክ ሠራተኞች አድማ ወደሌሎች ድርጅት ሠራተኞች ተዛምቶ የነበረ ሲሆን ጥያቄዎቹ ይዘታቸውና አድማሳቸው ሰፍቶ አብዛኞቹን ሠራተኞች ያካተተ አድማ በየካቲት 66 በኢሰአማ አማካይነት ሊደረግ ችሏል፡፡ ይህም የሠራተኞች አድማ በወቅቱ ሥልጣን ላይ የነበረውን ክፍል ቅስሙን ሰብሮታል፤ አርበድብዶታል፡፡ መምህራን የደሞዝ ጭማሪና እንዲሁም በወቅቱ የደሃውን ልጅ ከከፍተኛ ትምህርት የሚያግደውና ሴክተር ሪቪው በሚል ስም ተወጥኖ የነበረውን አግላይ ፖሊሲ እንዲሻር በመጠየቅ ታግለዋል፡፡ አርሶ አደሩ በተለያዩ ቦታዎች - በሐረር፣ በጭላሎ፣ ...ወዘተ - መሬት ለአራሹ እንዲሆን፤ ጭሰኝነት እንዲቆም፤ ...ወዘተ አመጽ አካሄዷል፡፡ ለዓመታት በተማሪዎችና በሌሎች አብዮታውያን ሲጠየቅና ትግል ሲካሄድበት የነበረው የመሬት ለአራሹ መፈክር በየካቲት 66 እንቅስቃሴ ያጎለበተና ያጠናከረ መፈክር ነበር፡፡ ታክሲ ነጅዎች የቤንዚን ዋጋ በመጨመሩ የሥራ ማቆም አድማ ሲያካሄዱ በተለያዩ እቃዎች የዋጋ ግሽበት የትራንስፖርት ዋጋ ጭማሪን ጨምሮ ሲሰቃይ የነበረው ሰፊው ሕዝብ ተመሳሳይ ጥያቄ በማቅረብ ከታክሲ ነጅዎች ጎን መሰለፉ የየካቲቱን ሕዝባዊ

እንቅስቃሴ ነዳጅ ሆኖ አቀጣጥሎታል። ቄሶች ለደሞዝ ጭማሪና ለኑሮ ሁኔታ መሻሻል ጥያቄዎች ሲያቀርቡ የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ከክርስቲያንና ከሌሎች ዕምነት ተከታዮች ወንድሞቹ ጋር በመሆን የሃይማኖት እኩልነት እንዲኖር፤ መንግሥትና ሃይማኖት እንዲለያዩ፤ የሙስሊሙ በዓላት በብሔራዊ ደረጃ እንዲከበሩ የሚሉትን ጥያቄዎች በማንገብ ታግሏል። በታኅሳስ 66 ቦረና በነበረው ጭቁን ወታደር የኑሮ ሁኔታን መሻሻልና የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄዎችን በማንሳት የተጀመረው አመጽ ወደ አዲስ አበባው አራተኛ ክፍለ ጦርና ወደ አየር ኃይል አባላት ቀጥሎም አስመራ ላይ ወደሚገኘው ሁለተኛ ክፍለ ጦር ተዛምቶ የነበረውን የፊውዳል ሥርዓት ለማርበድበድ ችሏል። በተለይ የሁለተኛ ክፍለ ጦር ወታደሮች ባቀረቡት የ23 ነጥብ ጥያቄዎች ውስጥ የአስተዳደር ለውጥ ጥያቄ የተካተተበት ስለነበር ሕዝባዊ አመጹ አድማሱ ሰፍቶ እንዲቀጣጠል አስተዋጽኦ አድርጓል። ተማሪዎች መሬት ላራሹ ይሰጥ፤ የሠራተኛው መደብ ጥቅም ይከበር፤ የብሔርና የጾታ እኩልነት ይስፈን እንዲሁም የባላባታዊ አገዛዝ ተወግዶ ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት የሚለውን መፈክር በማንገብ ተቃውሞ አሰምተዋል። አመጹን አንቀሳቅሰዋል። ከዓመታት በፊት የጀመረው የተማሪዎች የተቃውሞ እንቅስቃሴ የአጼውን መንግሥት መለኮታዊነት የሸረሸረ፤ የሕዝብ ተስፋና የትግል ስሜት እንዲንሰራራ ያደረገና ለየካቲት 66 እንቅስቃሴ እርሾ የነበረ መሆኑ ግልጽ ነው። የሕዝብ መብትና ጥቅም ይጠበቅ፤ መሬት ላራሹ ይሁን፤ ዴሞክራሲያዊና ሕዝባዊ ሥርዓት ይመስረት የሚሉት፣ ተማሪው የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር በመክፈል ለረዥም ጊዜ ሲታገልላቸው የነበሩ ጥያቄዎች የየካቲት አብዮት ደማቅ አካል ነበሩ። የወቅቱ ተማሪዎችና ወጣቶች ዛሬ አንዳንድ የግል ጥቅማቸውን ያስቀደሙና ሌላ አጀንዳ ያላቸው ሊከሷቸው እንደሚሞክሩት በሻዕብያና በጀብሃ ወይም በውጪ ኃይሎች አጀንዳ ሲሽከረከሩ የነበረ ሳይሆን የደኻው ወገናቸው በደል ያንገበገባቸውና የቆጠቆጣቸው፤ መንፈሳቸውን የረበሻቸው ከአንድ ጎሳ ወይም ቋንቋ ተናጋሪ ሳይሆን ከሁሉም ብሔረሰብ የተውጣጡ፤ ለሕዝብ ልዕልና፤ ለሀገር ሉዓላዊነት ለአንድነትና ለእኩልነት ራሳቸውን አሳልፎ ለመስጠት ዝግጁነታችውን ያስመሰከሩ፤ ሀገር በቀል ዓላማ ይዘው የተነሱ የአገሪቷ ውድ ልጆች ነበሩ። በ50ዎቹ መጀመሪያ ላይ ሥርዓቱን በመቃወም የጀመረው የተማሪው ትግል በየካቲት 66 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ውስጥም ግምባር ቀደም ሚና የነበረው መሆኑ አከራካሪ አይደለም። ከተማሪው እንቅስቃሴ አብራክ የተወለዱ በህቡዕ የተደራጁ እንደ ኢሕአፓ ዓይነት የፖለቲካ ድርጅቶችም በወቅቱ ገና ጨቅላ ስለነበሩ የየካቲቱን ሕዝባዊ አብዮት መርተው ዳር ሊያደርሱት ባይችሉም እንቅስቃሴው ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲይዝ፤ ተሰባስቦ እንዲጠናከር እንዲሁም ጥያቄዎቹ ከግልና ክልላዊ ጥያቄዎች ወጣ ብለው በአገር አቀፍና በስር ነቀል ለውጥ ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ በኩል ያደረጉት አስተዋጽኦ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም።

የየካቲቱን እንቅስቃሴ ልዩ ከሚያደርጉት ጉዳዮች ውስጥ አንደኛው ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያካተተ እንቅስቃሴ መሆኑ ነው። በጾታ፣ በእድሜ፣ በቀለም፣ በቋንቋ፣ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በሙያ፣ በሥራ መስክ፣ በመደብ፣ በመንደር፣ በክልል፣ … ወዘተ ልዩነት ሳይኖር ሁሉም ዜጋ የተሳተፈበት እንቅስቃሴ ነበር። ሴት ወንዱ፣ ወጣትና ሽማግሌው፣ ሠራተኛው፣ መምህራን፣ የቢሮ ሠራተኞች፣ ታክሲ ነጅዎች፣ አርሶ አደሮች፣ ሥራ አጦች፣ በዝቅተኛ ሥራ ላይ ያሉ ዜጎች፣ ሊስትሮዎች፣ በተለያዩ እርከን ላይ ያሉ ወታደሮች፣ የተለያዩ ብሔረሰብ አባላት፣ የተለያዩ ሃይማኖት

ተከታዮች፣ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ … ወዘተ በእንቅስቃሴው ተሳትፈዋል፤ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል፤ ታግለዋል፤ መስዋዕትነት ከፍለዋል። በእነዚህ ወገኖች የተባበረ ትግል ነው የባላባቱ ሥርዓት ተወጥሮ በመጨረሻ ሊገረሰስ የቻለው።

የየካቲቱ ሕዝባዊ አመጽ በዋና ከተማዋ ተቀጣጥሎ ይስፋፋ እንጂ በአዲስ አበባ ላይ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። አገር አቀፍ ይዘት ነበረው። በተከታዮቹ ሳምንታትና ወራት ሕዝባዊ እንቅስቃሴው ወደ ጅማ (ከፋ)፣ መቂ (ሸዋ)፣ ባሌ ጎባ (ባሌ)፣ አዲ ኡግሪ (ኤርትራ)፣ ድሬደዋ (ሐረር)፣ ደሴ (ወሎ)፣ አክሱም (ትግራይ)፣ እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች በመዛመት ሥርዓቱን አናግቶታል። በተለይ ጅማ ውስጥ ነዋሪው ሕዝባዊ ኮሚቴ በማቋቋም የጸጥታ ኃይሎችን በማስወገድና አስተዳዳሪውን በማባረር ጊዜያዊ የሆነ ሕዝባዊ አስተዳደር በመመስረቱ የሕዝብ ቁጣና ኃይል የማይበገር መሆኑን አስመክሯል። የእንቅስቃሴው አገር አቀፋዊነት ለየካቲት አብዮት አንዱ ጠንካራ ገጽታው ነው።

የካቲትን ልዩ የሚያደረገው ሁለተኛው ገጽታ በእንቅስቃሴው ውስጥ የተነሱት ጥያቄዎችና ትግል የተካሄደባቸው መፈክሮችጊዜያዊ ጥቅምን ማስጠበቅና ችግሮችን መቅረፍ ከሚሉት ውሱን ጥያቄዎች ሰፍተው ሥር ነቀል የሥርዓት ለውጥንና የዴሞክራሲያዊና ሕዝባዊ መንግሥትን ጥያቄዎች ያካተቱ መሆናቸው ነው። ከለልተኛና ግላዊ የሆኑ ጥያቄዎች በራሳቸው ክብደት ያላቸው ቢሆንም የሥርዓት ለውጥ በማምጣት በኩል የሚኖራቸው ሚና ኢምንት ነው። እንዲያውም የሥርዓቱ መሪዎች ለማስታገሻ አንዳንዶቹን ጥያቄዎች ሊመልሱ ይችላሉ። በታክሲ ነጅዎች የነዳጅ ዋጋ ቅናሽና በወታደሮች የተጠየቀው የደሞዝ ጭማሪና የኑሮ ሁኔታ መሻሻል መልስ አግኝተው እንደነበር የሚታወስ ነው። ይህም የየካቲቱ እንቅስቃሴ ጠንካራ ገጽታ ነበር። ለውሱን ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች ሳያረኳቸው የጥያቄውን አድማስ በማስፋትና በእርግጥም ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው የሥርዓት ለውጥ መሆኑን በመገንዘብ እንቅስቃሴውን ወደ ድል ሊያቃርብ የሚችለውን ጥያቄና መፈክር አንግበው እስከመጨረሻው ታግለዋል።

ጽናት ያለው ሥራ ግቡን ሊመታ እንደሚችል የየካቲቱ እንቃስቃሴ ያስመሰከረ ሲሆን ይህም የእንቅስቃሴው ጠንካራው ገጽታ መሆኑ የታወቀ ነው። በተለያዩ ጊዜያት ገዥው ክፍል የተወሰኑትን ጥያቄዎች በመመለስም ሆነ የኃይል እርምጃ በመውሰድ፤ ከሥራ በማስወጣትም ሆነ በማስፈራራት እንቅስቃሴውን ለማኮላሸት ጥረት አድርጓል። የእንቅስቃሴው ተዋኒያን የነበሩት ሕብረተሰብ ክፍሎች የገዥው ክፍል በሰጣቸው ቅንጥብጣቢ መልሶች ሳይረኩ፤ በጥቅማቸው ሳይደለሉ ወይም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ሳይደናገጡና ተስፋ ሳይቆርጡ ኃይላቸውን አስተባብረው፣ በሥር ነቀል የለውጥ ጥያቄ ላይ አተኩረው ትግል በማካሄዳቸው ማንም አይደፍረውም ሲባልለት የነበረው ሥርዓት ሊገረሰስ ችሏል። እንቅስቃሴው በጽናት በመቀጠሉ ምክንያትም የሥርዓቱ ተከላካይና ጠባቂ የሆኑት ሳይቀሩ የኋላ ኋላ እንቅስቃሴውን ተቀላቅለዋል። ሰልፈኛውን በቆመጥና በዱላ ሲደበድቡ የነበሩ፤ በጥይት ሲገድሉ የነበሩ የጸጥታ ኃይሉ አባላት ከሰልፈኛው ጋር አብረው ብሶታቸውን በሥርዓቱ ላይ ገልጸዋል። ይህም የእንቅስቃሴው ጠንካራው ገጽታ ነበር።

ሆኖም እንቅስቃሴው ድክመት አልነበረውም ማለት አይቻልም። ከላይ እንደተጠቀሰው ምንም እንኳን ሕዝባዊ አብዮቱ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ያካተተ መሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ቢሆንምና እንዲሁም በህቡዕ የተደራጁ እንደኢሕአፓ ያሉ ተራማጅ ኃይሎች በእንቅስቃሴው በመሳተፍም ሆነ አቅጣጫ በማስያዝ በኩል ያደርጉት ጉልህ አስተዋጽኦ አከራካሪ ባይሆንም፣ ወደተጠበቀው ግብ የሚያደርስ ጠንካራ የሆነ የተደራጀ ኃይል እንቅስቃሴውን አልመራውም። በመጨረሻም ለስድስት ወር ያህል በርካታ ኢትዮጵያውያን የተንቀሳቀሱበት፤ የታገሉበትና የተዋደቁለት አብዮት የአፄውን ሥርዓት ለማዳከምና ለማስለል ቢችልም ሥልጣን በሕዝብ እጅ ሳትገባ በወታደሩና በታጠቀው ክፍል ልትሞጨለፍ በቅታለች።

በየካቲት 66 የተነሱት ጥያቄዎች መልስ ባለማግኘታቸው ላለፉት አርባ ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ በተከታታይ በአምባገነንና ፈላጭ ቆራጭ ቡድኖች ሲጨፈጨፍ፣ ሲበደልና ሲጨቆን ቆይቷል። በየካቲት 66 የአፄውን ሥርዓት በመገርሰስ ሥልጣንን ከሕዝብ ነጥቆ የራሱ ያደረገው የወታደሮች ጥርቅም በመጀመሪያ ራሱን ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ በኋላም ኢሰፓ ብሎ በማደራጀት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ጨፍጭፎ፤ ሕዝቡን አሰቃይቶና አድህይቶ፤ አገሪቷንም የጦርነት አውድማ አድርጎ ከቆየ በኋላ የባዕዳንን ትብብርና ድጋፍ ባገኙት በወያኔና በሻዕቢያ ድል ሆኖ ከሥልጣን ሊወገድ ችሏል። ደርግን የተካው ወያኔም አገሪቷን በጎሳ ክልሎች ከፍሎ የአንድ ዘር የበላይነትን በማስፈን የሕዝቡን መብት ገድቦና አፍኖ የአገሪቷን ሀብት በመበዝበር ሕዝቡን እያሰቃየ አለ።

የካቲት ዋነኛውና ውስጣዊ ባህሪው በዚያን ወቅት ያቀጣጠለው ትግል ህያው ሆኖ መኖሩ ነው። በየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት ወቅት ሕዝቡ "ሕዝባዊ መንግሥት ይመስረት፤ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቹ ይከበሩ፤ መሬት ላራሹ ይሁን ጭሰኝነት ይወገድ፤ የብሔርና ብሔረሰቦች እኩልነት ይኑር፤ መንግሥት በሃይማኖት፥ ሃይማኖት በመንግሥት ውስጥ ጣልቃ አይግባ፤ የሃይማኖቶች መብትና ነጻነት ይከበር፤ ሙስናና በሥልጣን መባለግ ይወገድ፤ ነፃ ትምህርትና ህክምና ለደሃው ይሰጥ፤ የሸቀጦች ዋጋ ቁጥጥር ይኑር" የሚሉትን ዋና ዋናና መሠረታዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ ታግሏል። እነዚህ ጥያቄዎች አሁንም ፈጠው ያሉ መሆናቸውን ለመረዳት አዋቂነትን አይሻም። ዛሬም ሥልጣን ከሕዝብ የሚመነጭበት ሁኔታ አልተፈጠረም። ወያኔ በይስሙላና በማስመሰያ ምርጫ ሥልጣን ላይ ወጣሁ ቢልም ዛሬም ሥልጣን በሕዝብ በተመረጠና ሕዝብ በሚቆጣጠረው ክፍል ሳይሆን ከአንድ ብሔር በተውጣጣ አፋኝና አምባገነን ቡድን እጅ ነው ያለው። ዛሬም የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶቹ እንደተጣሱ ናቸው። ዛሬም የንግግር፣ የጽሁፍ የመሰብሰብ የመደራጀት፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነቶች ገደብ እንደተጫነባቸው አሉ። ዛሬም ወያኔን መተቸትና መቃወም ያሳስራል፤ ያስቀጣል፤ ከስራ መባረር ያስከትላል። ከ30000 በላይ የሚሆኑትንና በእስር እየማቀቁ ያሉትን ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞችና አርሶ አደሮች ለአብነቱ መጥቀሱ የጉዳዩን አሳሳቢነት ያረጋግጣል። ዛሬም የአንድ ቡድን አምባገነንነት እንጅ የሕግ የበላይነት የለም። ዛሬም መሬት ለአርሶ አደሩ አልሆነም። ወያኔ በመንግሥት ስም መሬትን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የሚበዘብረው ሳይበቃ፤ አርሶ አደሩን ከመሬቱ ላይ በማባረር ለባዕዳን ባለሀብቶች መሬትን መቸብቸብ

ከጀመረ ዓመታት አስቆጥሯል። እንዲያውም አገሪቱን ለውጭ ከበርቴዎች የመሬት ቅርምት ገነት አድርጎላቸዋል። ለጎረቤት አገሮችም ለፖለቲካና ለሌሎች ጥቅሞች ሲል መሬትን አሳልፎ ይሰጣል። ዛሬም ብሔርና ብሔረሰቦች መብታቸው ተጠብቆ በእኩልነትና በአንድነት እንዲኖሩ አልተደረገም። ይብስኑ ከአብራክህ የወጣን ነን፤ ላንተ ጥቅም የቆምንና የመብትህ ተከላካይ ነን በሚሉ ቡድኖች እየተበዘበዙ፤ እየተረገጡና እየተበደሉ ይገኛሉ። በአንድነት ተነስተው መብታቸውን እንዳያስከብሩ በመካከላቸው ጥላቻና መራራቅ እንዲፈጠር ወያኔ በረቀቀ ዘዴ መርዙን እየረጨ ይገኛል። ዛሬም ወያኔ የሃይማኖት ተቋሞችን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የሥርዓቱ መጠቀሚያና አገልጋይ ለማድረግ የሚወጥናቸውና በተግባር የሚያውላቸው እኩይ ተግባሮች በገሃድ የሚታዩ ናቸው። የኦርቶዶክሱን ሃይማኖት ፓትርያርክ ከመመደብ ጀምሮ ተቋሙን ከታች እስከላይ ለመቆጣጠር የፈጸመው ድርጊትና እንደዋልድባ ዓይነቱንና ሌሎችን የቤተክርስቲያን ንብረቶች ለመዝረፍ ያደረገው ጥረት የክርስቲያን ተከታዮችን ጥላቻና ተቃውሞ ያስከተለበት ሲሆን የእስልምናውን ሃይማኖት ተቋም በራሱ ደጋፊዎችና ካድሬዎች ለመቆጣጠር የወሰዳቸው እርምጃዎችና የአካሄዳቸው የአፈና ተግባሮች የሙስሊሙ ወገኖቻችንን ተቃውሞ በመቀስቀስ ከፍተኛ ትግል እያካሄዱበት ይገኛል። ዛሬም የሀገሪቷ አንጡራ ሀብት ሥልጣን ላይ ባሉት የወያኔ ዘረኛ ቡድን አባላትና አሽከሮቹ እየተበዘበዘ ነው። የወያኔ ቀንደኛ አባላት ኤፈርት በሚባለው የማፊያ ድርጅት አማካይነትና እንዲሁም ቀጥታና ተዘዋዋሪ በሆኑ ሌሎች መንገዶች የአገሪቷን ሀብት ምንጥር አድርገው እየዘረፉ ሲሆን በተለያዩ የአስተዳደር የሥልጣን እርከን ላይ ያሉ አባላትና ተባባሪ አሽከሮች በሙስናና በዝርፊያ አገሪቷንና ሕዝቡን እያራቆቱ ይገኛሉ። ዛሬም የትምህርት ይዘታውና የሕክምናው አገልግሎት በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው። ዛሬም ሕዝባችን በዕቃዎች ዋጋ ግሽበት፥ በኑሮ ውድነት፥ በአገልግሎት (መብራት፣ የመጠጥ ውሃ፣ … ወዘተ) እጥረት እየተሰቃየ ይገኛል። ባጠቃላይ የዛሬ አርባ ዓመት የሕዝብ ብሶት ሆነው፤ ሕዝቡን አስቆጥተውና አሳምጸው የአፄውን ሥርዓት እንዲገረሰስ ያደረጉት ጥያቄዎች በአሁኑ የአገራችን ሁኔታ ህያው ሆነው ይታያሉ።

ለ23 ዓመት ሲጠራቀም የቆየው የሕዝብ ብሶት ዛሬ ወደጣሪያው እየተጠጋ ነው። የሕዝብ በደልና ብሶት፤ የሕዝብ እንባና ዋይታ እየተከማቸ ከሄደ የሕዝብን ቁጣና አመጽ ማስከተሉ የማይቀር መሆኑን ከዓለም ታሪክ ተመክሮዎች ሌላ የአገራችን የየካቲት 66ቱ ሕዝባዊ አብዮት አረጋግጦልናል። የሕዝብን ቁጣ ሊያበርድ፤ ብሶቱንም ሊያሚሽሽ የሚችል ሁኔታ እስካልተፈጠረ ምንም እንኳ ቀንና ጊዜውን መተንበይ ባይቻልም ዳግማዊ የካቲት መምጣቱ አይቀሬ ነው። የተበደለ ሕዝብ ማመጽ ምርጫው ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ስለሆነ በደልና ችግር ሲበዛበት፣ ሁኔታው ሲጠብበት አመጽ ማካሄዱ የሚጠበቅ ነው። በየቦታው የሚደረጉት የተቃውሞ ሰልፎች፤ በስብሰባዎች፥ በጸሎት ቤቶች፥ በትምህርት ቤቶች፥ በመስሪያ ቤቶች፥ …ወዘተ የሚገለጹት የሕዝብ እሮሮዎችና ብሶቶች፤ በጋዜጣ በበራሪ ወረቀቶች የሚጻፉት የተቃውሞ መልእክቶች፤ በየአደባባዩ የሚጻፉት መፈክሮች፤ በከተማና በገጠር የሚታዩት የእምቢታ እንቅስቃሴዎች ለመጭው አርእድ አንቀጥቅጥ ሕዝባዊ አመጽ ፍንጮችና ምልክቶች ናቸው ቢባል ከእውነት የራቀ አነጋገር አይሆንም።

ሕዝባዊ አመጽን መተንበይና በፈለጉት ጊዜ መለኮስ ባይቻልም የሕዝቡ የብሶት እንቅስቃሴን ማጠናከርና ከየካቲት 66ቱ ሕዝባዊ አመጽ ድክመትም ሆነ ጥንካሬ ትምህርት በመቅሰም ሕዝባዊ እንቅስቃሴው ግቡን እንዲመታ ማድረግ ለአገርና ለወገን ከሚያስቡ ታጋይ ዜጎች የሚጠበቅ ግዴታ ነው። በተለያዩ አካባቢዎች የሚካሄዱትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ማጠናከር ማቀናበርና ወደ ግብ እንዲያመሩ ማድረግ ጊዜው የሚጠይቀው ግዳጅ ነው። የየካቲት 66 አብዮት ከተወልን ቅርሶች መካከል አንደኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በእድሜ፣ በጾታም፣ በቋንቋ፣ በብሔረሰብ፣ በሃይማኖት፣ ...ወዘተ ሳይለያይ እጅ ለእጅ ተያይዞ በአንድ ላይ በሥርዓቱ ላይ መነሳቱ ነው። እያንዳንዱ ልዩነቶችን በሁለተኛ ደረጃ አስቀምጦ ያንዱ ቁስል አንዱ እየተሰማው፤ ብሶታችሁ ብሶቴ ነው፤ ችግራችሁ ችግሬ ነው ብሎ ከሌላው ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ የጋራ ጠላት በሆነው ሥርዓት ላይ መነሳቱ የሕዝብን ትስስርና አንድነት አጠናክሯል፤ ከንዱንም አፈርጦሚል። ወያኔ በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተቀምጦ ኢትዮጵያን መቦጥቦጥ እንዲያመቸው አገሪቷን በቋንቋና በብሔረሰብ ክልሎች ከፋፍሎ አንዱን በሌላው ላይ፤ የአንዱን የእምነት ተቋም በሌላው ላይ፤ ... ወዘተ በማስነሳት በየጊዜው የሚጎነጉነውንና የሚገምደውን የሴራ ገመድ በጣጥሰን አንድነታችንን አጠናክረን የጋራ በዳያችን፤ የጋራ ጠላታችን በሆነው በወያኔ ላይ መነሳት ይጠበቅብናል። ባሁኑ ጊዜም መከፋፈልን ማስወገድና ከንድን ማስተባበር አስፈላጊነቱ የማይታበል ነውና ይህ እውን ይሆን ዘንድ በሕዝብ ጎራ ውስጥ ሆነው ክፍፍልን የሚያነግሱትን ማጋለጥና ከጥቅም ውጪ ማድረግ ወሳኝ ነው። አንድነታችን ተጠብቆ ትግላችን ሊሰምር የሚችለው በቋንቋ፣ በብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ ... ወዘተ አለመለያየታችን ብቻ ሳያሆን ወያኔን ከመጣበት ሕብረተሰብ ነጥለን ተጠያቂ ስናደርገውና ቡድኑን ብቻ ኢላማ አድርገን ስንረባረብ ነው።

የየካቲት 66ቱ አብዮታዊ እንቅስቃሴ የአመራር ክፍተት ስለነበረ የሕዝብ ትግል ኢላማውን ለመምታት አልቻለም፤ ሥልጣንም በሕዝብ እጅ ሳትገባ በሌላ አፋኝና ጨቋኝ ኃይል ልትወሰድ ችላለች። በመጭው ዳግማዊ የካቲት የሕዝብ ትግልና መስዋዕትነት ከዳር እንዲደርስና ፍሬ እንዲያፈራ የተደራጀ፣ የተጠናከረ፣ ቁርጠኛና አስተዋይ የሆነ አስተባባሪና አቅጣጫያ ሰጭ አመራር ለመስጠት መዘጋጀት አለበት። በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ይህ ሃላፊነት የሚወድቀው በአንድ ድርጅት ወይም ቡድን ላይ ሳይሆን የአገሪቱን ሉዓላዊነት ለመጠበቅና ሕዝቧንም የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል፤ አደራጅተናል፤ እንመራለን በሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ሁሉ ነው። በየጊዜው የሚገኙ ድሎችም ሽንፈት እንዳያጋጥማቸውና የሕዝብን ስሜት እንዳያቀዘቅዙ ሕዝባዊ ኃይል ማዘጋጀትም የማያልፉት ግዳጅ ነው። ደጋግመን እንደገለጽነው ተደራጅተናል ትግሉን ለመምራት ብቃት አለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች አቋማቸውን አስተካክለው፤ ጽናትና አይበገሬነትን ተጎናጽፈው፤ በጥቃቅን ልዩነቶች ሳይለያዩ፤ በጥቅማ ጥቅምና በአጭር እይታ ሳይታለሉ፤ ኃይላቸውን አስተባብረው አይቀሬውንና መጭውን ሕዝባዊ አብዮት ለመምራትና የሕዝቡን ትግል ከዳር ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የሚተባበር እስካለ ድረስ ኢሕአፓ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በተግባር እንዳስመሰከረው ሁሉ አሁንም ለመተባበርና የሚፈለገውንና የሚጠበቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁነቱን በተደጋጋሚ ገልጿል፤ አሁንም ይገልጻል። ይህንን ክፍተት ለመሙላት በኢሕአፓ በኩል ከምንጊዜውም በበለጠ በሚቻለው ሁሉ ጥረት ለማድረግ ቆርጦ የተነሳ ሲሆን በሀገር

ቤት በተከታታይ ያደረጋቸውና አሁንም እያከናወናቸው ያሉት የቅስቀሳና የማደራጀት ሥራዎች ለዚህ ምስክሮች ናቸው። ብሶትና ቁጣ የሚቀሰቅሰው የሕዝብ ኃይል የወታደርና የመሣሪያ ጋጋታ የሚቋቋመው አለመሆኑን የካቲት 66ና ሌሎች የዓለም አብዮቶች ያስመሰከሩት ስለሆነ በዳግማዊ የካቲትም ይህ እንደሚደገም በእርገጠኛነት መናገር ይቻላል። ቁርጠኛና ትክክለኛ አመራር ካገኘም ሥልጣን ከሕዝብ የሚመነጭበት ሥርዓት እውን እንደሚሆን ጥርጥር ሊኖር አይገባም።

በሕዝብ ትግልና መሰዋዕነት፣
ዳግማዊ የካቲት ዕውን ይሆናል!